# ADDA BILISUMMAA OROMOO

**OROMO LIBERATION FRONT** | **جبهة تحرير اورومو**

Gaafa: 26/12/2015
Date: تاريخ

Lakk.: 19/stm - abo/2015
No.: رقم

## የወያኔ መሪዎች ለፈሰሰው ለእያንዳንዱ የኦሮሞ ዜጎች የደም ጠብታ ተጠያቂዎች ናቸው

*የኦሮሞ ነጻነት ግንባር መግለጫ*

የኦሮሞ ህዝብ መብቱን ለማስከበርና ለብሄራዊ ህልውናው ዋስትና እያካሄደ ባለው ፍልሚያ በተከፈተበት ጠላታዊና የሽብርተኝነት ዘመቻ እየከፈለ ያለው መስዋዕትነት እጅግ ከባድ ነው።
ወያኔ ለኦሮሞ ህዝብ ያለው ንቀትና የሚፈጽመው ገደብ-የለሽ ጭቆናና ኣፈና፡ የህዝባችንን ማንነት ለማጥፋት እያካሄደ ያለው ዘመቻ እየከፋ በሄደ ቁጥር ህዝባችን ትዕግስቱን በመጨረሱ በመላው ኦሮሚያ ውስጥ በኣንድነት ተነስቶ በኣንድ ድምጽ ተቃውሞውን በሰላማዊ መንገድ በማሰማት ላይ ይገኛል።

የወያኔ መንግስት የኦሮሞ ህዝብ በሰላማዊ መንገድ እያቀረበ ላለው ጥያቄ ትክክለኛና ሰላማዊ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ እንደልማዱ የባዕዳንን ወረራ ለመከላከል የተደራጀውን የሃገሪቷን ጦር ሃይል በሰላማዊና ንጹሃን ዜጎች ላይ በማሰማራት ሰላማዊውን ተቃውሞ ለማቆምና ለማፈን እየሞከረ ነው። ህዝቡ ግን በተሰማራበት የጠላት ጦር ሳይንበረከክ ኣመጹን በተለያየ መልኩ ቀጥሏል።

ይከሰታል ተብሎ በማይጠበቅና በማይታሰብ ሁኔታ እንደጎርፍ መላውን ኦሮሚያ ባጥለቀለቀው ሰላማዊ የተቃውሞ ማዕበል የተደናገጠው የወያኔ መንግስት ዘግናኝ እርምጃ በመውሰድ ይህንን ተቃውሞ ለማፈን እየፈጸመ ባለው የጭካኔና ኣረመኔያዊ ግድያ፡ የንጹሃንን ደም በማፍሰስ ዓላማቸውን በሃይል እውን ከሚያደርጉ ኣሸባሪዎች ጎራ መሰለፉን ይበልጥ ኣረጋግጧል።

ታህሳስ 15 ቀን 2015ዓም በሚዲያው በኩል በኦሮሞ ህዝብ ላይ በግልጽ ካሳወቀው የወረራ ኣዋጅ በኋላ እየወሰደ ባለው ዘግናኝ እርምጃ ለኦሮሞ ህዝብ ያለውን በጠላትነትና ጥላቻ ላይ የተመሰረተ ኣመለካከት እስከ ኣሁን ያላወቁት እንዲያውቁ ኣስችሏል። እየወሰደ ያለው እርምጃም ከኣሸባሪዎች እርምጃ ኣንዳች ልዩነት የሌለው መሆኑን ያለጥርጥር ማረጋገጥ ይችላል።

ኣክራሪ ቡድኖች ሰላማዊውን ህዝብ እኔን ደግፍ ወይንም የኔን ፍላጎት ኣሟላ በማለት ኣስገድደው የተቃወማቸውን ኣልያም ፍላጎታቸውን ያላሟላውን እንደሚያርዱት ሁሉ፡ ወያኔም ንጹሃን የኦሮሞ ዜጎችን በመግደል በሃይል ፍላጎቱን ለማሟላት እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ባሰማራው የጦር ሃይሉ እያሳየ ነው።

P.O. Box 6973 Asmara, Eritrea Tel 2911 110236 Email: Caalchis@gmail.com, *www.oromoliberationfront.org*

ኣሸባሪ ቡድኖች ህዝቡን በሃይማኖት በመለያየት የራሳቸውን በማስቀደም ሌላኛው እንዲጠፋ ወይንም ኣማኞች ላይ ዘግናኝ እርምጃ በመውሰድ እንደሚታወቁ ሁሉ፡ የወያኔ መንግስትም የኦሮሞ ዜጎችን በብሄር ለይቶ ከሌሎች ህዝቦች በመነጠል በመግደል፣ በማሰርና በማሳደድ ላይ ይገኛል።
አሸባሪዎች መሳሪያ-ኣልባና ምንም ጉዳት ሊያደርሱ የማይችሉ ዜጎችን በጭካኔ እንደሚፈጁት፡ የወያኔ መንግስትም እናትና ልጅን በኣንድ ላይ የሚገድል መንግስት ነው።

ኣሸባሪዎች ለሰው ልጆች ክብርና ፍቅር የሌላቸው ከመሆኑም በላይ ዘግናኝና ኣስደንጋጭ እርምጃ በመውሰድ እኩይ ኣላማቸውን ከግቡ ለማድረስ እንደሚጥሩ ሁሉ፡ የወያኔ ኣናሳ ቡድንም ንጹሃንን ገድሎ ክቡር የሰው ኣካል ክብር በሌለው ሁኔታ በየጢሻውና መንገዱ በመጣል፣ ማንነቱን ማወቅ በማያስችል ሁኔታ ቆራርጦ በመግደልና በማቃጠል ቀብር ከልክሎ ኣረመኔያዊ የጭካኔ ድርጊት በመፈጸም ከኣሸባሪዎች ጎራ ተሰልፏል።

የወያኔ መንግስት እስከኣሁን ድረስ በፈጸመው በዚህ ድርጊቱ ከ85 በላይ ንጹሃን ዜጎችን መግደሉ ተረጋግጧል። በሺዎች የሚቆጠሩት በጥይትና በድብደባ ለኣካላዊ ጉዳት ተዳርገዋል። በግልጽ በሚታወቁና በማይታወቁ እስርቤቶች ውስጥ ኣጉሮ እያሰቃያቸው የሚገኙት ዜጎች ቁጥር በኣስር ሺዎች ይቆጠራል።

በኦሮሞ ህዝብ ላይ እየፈጸመ ባለው በዚህ ሁሉ ድርጊቱ ያልረካው የወያኔ ኣናሳ ቡድን የኦሮሞ ህዝብን ኣዋቂና ምሁር ለማሳጣት እንዲሁም በሃገሪቷ ህገ-መንግስት ስር በሰላማዊ መንገድ ትግል ለማካሄድ ቃል የገቡትን ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ የሆነው የኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረስ(ኦፍኮ) ኣመራሮች እነኣቶ በቀለ ገርባ፣ ደጀኔ ጣፋና በተለያዩ ደረጃ ላይ የሚገኙትን ኣመራሮችና ኣባላትን ከመላው ኦሮሚያ ውስጥ ለቅሞ ወህኒ በመወርወር የሽብርተኝነት ድርጊቱን በስፋት ቀጥሏል።

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር የወያኔ መንግስት በኦሮሞ ህዝብ ላይ እየፈጸመ ያለውን ግድያ፣ ድብደባና እስራት በጽኑ ያወግዛል። የኦሮሞ ነጹሃን ዜጎች እንዲገደሉ ህገ-ወጥ ትዕዛዝ ያስተላለፉትና ይህንኑ ህገ-ወጥ ትዕዛዝ ተግባራዊ ያደረጉ ሃይሎች ለህግ እንዲቀርቡና እየተፈጸመ ያለው የኣሸባሪነት ተግባር በገለልተኛ ወገን እንዲመረመር ይጠይቃል። የኣለም ማህበረሰብና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የሚታገሉ ተቋማት ሁሉ በኢትዮጵያ ውስጥ በጅምላ እየተጣሰ ላለው የዜጎች ብሄራዊና ሰብዓዊ መብቶች ተጠያቂዎች የሆኑትን ለፍርድ በማቅረቡ ሂደት የሚጠበቅባቸውን ድርሻ እንዲያበረክቱ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ማስታወስ ይወዳል።

**ድል ለኦሮሞ ህዝብ!**

**የኦሮሞ ነጻነት ግንባር**
**ታህሳስ 26 ቀን 2015ዓም**